የደቀ መዛሙርት መርሖዎች

# የትምህርቱ መሰረታዊ ሃሳቦች

## ኢየሱስ ክርስቶስ ማን ነዉ?

## ትምሕርት 1፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ማን ነዉ?

ከአንድ ሰዉ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ስትገናኝ፤ ምን ዓይነት መረጃዎችን ነዉ ስለእርሱ ማወቅ የምትፈልገዉ? አንድ ጓደኛህን ከሌላ አዲስ ሰዉ ጋራ ለማስተዋወቅ ስትሞክር፣ ምን ዓይነት መረጃዎችን ተጠቅመህ ነዉ በደንብ እንዲግባቡ የምታደርገዉ? እነዚህን ጥያቄዎች በጥንቃቄ ማጤን፥"ኢየሱስ ክርስቶስ ማን ነዉ?" የሚለዉን ርዕሰ ጉዳይ ብሩህ በሆነ አእምሮ እንድትመለከት ይረዳሃል። በትክክል እርሱን ለማወቅ፥ ስለእርሱ ምን ማወቅ ትፈልጋለህ? በዕለት ተዕለት ኑሮህ፥ በዙሪያህ ያሉትን ሰዎች፥ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋራ እንዴት ነዉ የምታስተዋዉቃቸዉ?

ታዋቂዉ እንግሊዛዊ ፀሐፊና የሃይማኖት ሊቅ (ቴዎሎጂያን)፥ሲ. ኤስ. ሌዊስ፥ ስለኢየሱስ ማንነት በምፀት ሲናገር፤ "መጽሐፍ ቅዱስን በምናነብበት ጊዜ ኢየሱስ ያደረጋቸዉንና የተናገራቸዉን ስናነብ፤ አንድ ድምዳሜ ላይ መድረስ የግድ ነዉ። ኢየሱስ ክርስቶስ አንድም እብድ፥ወይም ዉሸታም፥ ወይም ደግሞ እዉነተኛ ጌታ ነዉ" አለ። አንተስ፥ኢየሱስ ክርስቶስ ማን ነዉ ትላለህ?

ኢየሱስ ማን ነዉ ለሚለዉ ጥያቄ ብዙ ሰዎች፥ ኢየሱስ በእርግጥ እዉነተኛ ሰዉ ነዉ፤ እንዲሁም ታላቅ መምህር ነዉ ብለዉ እንደሚያምኑ መስማት የተለመደ ጉዳይ ነዉ። ሌሎች ደግሞ ምናልባት ነቢይ ነበር ይላሉ። ነገር ግን ኢየሱስ ስለራሱ ማንነት የተናገረዉ ከእነዚህ ሁሉ የተለየ ነበር። ኢየሱስ ማን ነዉ የሚለዉ ጭብጥ፥ ከምንም በላይ ልትደርስበትና በግልፅ ልታዉቀዉ የሚገባህ ግንዛቤ ነዉ። እንዲያዉ እንደዋዛ ስለ ኢየሱስ ማወቅ ብቻዉን ለድነት አያበቃም። ስለዚህ የኢየሱስን ማንነት ከመሠረቱ መረዳት ለግል ሕይወትህ የእምነት ጉዞ መልካም የመነሻ ነጥብ ነዉ። ለራስህ ግንዛቤና ሌሎችን ወደ ኢየሱስ ፍቅርና ክብር ለመጥራት ስትዘረጋ፥ በቂ ዝግጅት ለማድረግ ይረዳሃል።

መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ኢየሱስ ራሱን ማን ብሎ ኢንደጠራ እንማራለን። ኢየሱስ በምድር ላይ በኖረበት ጊዜ የሠራቸዉን ነገሮች በማጥናት ደግሞ፤ ኢየሱስ ማን እንደሆነና፣ ምንስ ለማከናወን እንደመጣ ሰፊ ግንዛቤ እንጨብጣለን።

መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ኢየሱስ ራሱን ማን ብሎ ኢንደጠራ እንማራለን። ኢየሱስ በምድር ላይ በኖረበት ጊዜ የሠራቸዉን ነገሮች በማጥናት ደግሞ፤ ኢየሱስ ማን እንደሆነና፣ ምንስ ለማከናወን እንደመጣ ሰፊ ግንዛቤ እንጨብጣለን።

አብዛኛዉን ጊዜ፡- በልጅነት ከተማርናቸዉ እዉቀቶች ይሁን፤ ወይም ከወላጆቻችን እና ካደግንበት ማኅበረሰብ እምነት የተነሳ፤ በቀላሉ ከልባችን ተቀብለን ለማመን የምናመነታባቸዉ ከባድ እዉነቶች በመጽሐፍ ቅዱሳችን ዉስጥ ይገኛሉ። ይሁን እንጂ፥ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን የምናምን ከሆነ፤ አንብበን ከመልእክቶቹ ጋራ መስማማት፤ ብሎም እምነታችንን ቃሉ ከሚነግረን እዉነታዎች ጋራ ማጣጣም ይጠበቅብናል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን የምንቀርበዉ የነበረንን ቁንፅል ግንዛቤ ይዘን፣ እኔ ልክ ነኝ በሚል ስሜት ከሆነ፣ ፍፃሜአችን ግራ መጋባትና ተስፋ መቁረጥ ይሆናል።

“እርሱም፦ እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው። 'ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ፦ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ'”

(ማቴዎስ 16:13-16)

ጥበብና መረዳትን እንዲሰጠን ወደ እግዚአብሔር መጸለይ፤ በእዉነት ኢየሱስ ማን እንደሆነ ለመረዳት እጅግ ወሳኝ ነዉ። መጽሐፍ ቅዱስ እዉነት መሆኑን አምነን የምንቀርበዉ ቢሆን፤ ከዚያም ብናነብ፥ብናጠና እና የቀድሞዉ አስተሳሰባችንና እምነታችን የተሳሳተ ነበር በማለት ትክክለኛዉን ለመስማት መልካም ፈቃድ ብናሳይ፤ በእርግጥ እግዚአብሔር ራሱን ይገልጥልናል።

ወንጌሎችን በጥልቀት ማንበብ፥ የኢየሱስን ድርጊቶችና ባሕርያት ያሳይሃል። ኢየሱስ ብዙ ታላላቅ ተአምራቶችን አድርጎአል። ድንቅ ጥበቦችንም ተናግሮአል። ሰዎችን ወደዳቸዉ በምሕረትና በርኅራኄም፥አገለገላቸዉ። እንዲሁም አለ፡-እኔ የአብ (አባት) የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ፤ ጨምሮም እኔ ክርስቶስ ነኝ፤ እኔ መሲሁ ነኝ አለ። እስቲ አንድ አፍታ ቆም ብለን እንመርምር፡- ኢየሱስ ዋሽቶ ነበር? ግራ ተጋብቶስ ተምታትቶበት ነበር? ወይንስ ሆነ ብሎ ሕዝቡን ወደ ተሳሳተ የእምነት አቅጣጫ ይመራቸዉ ነበር?

ከዕለታት አንድ ቀን ኢየሱስ ቂሣርያ አገር ላይ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ ሲል ጠየቃቸዉ:- “'ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆነ ይሉታል? ብሎ ጠየቀ። እነርሱም:- አንዳንዱ መጥምቁ ዮሐንስ፥ ሌሎችም ኤልያስ፥ ሌሎችም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ አሉት” ይህ አስደናቂ ጉዳይ ነዉ።

ኢየሱስ ምድር ላይ በኖረበት ጊዜ የነበሩ ሰዎችም፤ ታላቅ መምሕር ነዉ፤ ወይም ደግሞ ነቢይ ነዉ ብለዉ ያስቡ ነበር። በመጨረሻም ኢየሱስ የቅርብ ተከታዮቹ ማን እንደሚሉት ማወቅ ፈለገ፡- “እርሱም፡- እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው። ’ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ፡- አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ’” (ማቴዎስ 16:13–16) ኢየሱስም ይቀጥልና ጴጥሮስን ከምላሹ የተነሳ የተባረከ መሆኑን ይነግረዋል። ኢየሱስን መከተል፥ማገልገል፥መታዘዝና፥ አብሮ መሥራት ብቻዉን በቂ አልነበረም። ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ በእዉነት ማን እንደሆነ ማወቅ ይጠበቅባቸዉ ነበር። ለጴጥሮስ ከምንም በላይ ከፍተኛዉና ጠቃሚ እዉቀቱ፤ ኢየሱስ፥ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ማወቁ ነበር።

አንተም ኢየሱስን በእውነት ለማወቅ የምትጥር ከሆንክ፤ አይዞህ ብቻህን አይደለህምና አትጨነቅ። ብዙ ሰዎች እነርሱ ትክክል ነዉ ብለዉ በሚያስቧቸዉና፤ መጽሐፍ ቅዱስ እዉነት ነዉ ብሎ ከሚናገረው መካከል ሆነዉ፥ መወሰን ተስኖአቸዉ ሲታገሉ ነዉ ራሳቸዉን የሚያገኙት። አንዳንድ ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ጌታ ኢየሱስን እንዲያገኙ እየረዳሃቸዉ ከሆንክ፤ ሃሳባቸዉን በነፃነት እንዲናገሩና ጥያቄዎቻቸዉም እስኪመለሱላቸዉ ድረስ በፍቅርና በትእግስት ተሸከማቸዉ።

አንተም ኢየሱስን በእውነት ለማወቅ የምትጥር ከሆንክ፤ አይዞህ ብቻህን አይደለህምና አትጨነቅ። ብዙ ሰዎች እነርሱ ትክክል ነዉ ብለዉ በሚያስቧቸዉና፤ መጽሐፍ ቅዱስ እዉነት ነዉ ብሎ ከሚናገረው መካከል ሆነዉ፥ መወሰን ተስኖአቸዉ ሲታገሉ ነዉ ራሳቸዉን የሚያገኙት። አንዳንድ ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ጌታ ኢየሱስን እንዲያገኙ እየረዳሃቸዉ ከሆንክ፤ ሃሳባቸዉን በነፃነት እንዲናገሩና ጥያቄዎቻቸዉም እስኪመለሱላቸዉ ድረስ በፍቅርና በትእግስት ተሸከማቸዉ።

የናዝሬቱ ኢየሱስ፥ ልክ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደተፃፈዉ፤ በሕይወት መኖሩ፥ መሞቱና፥ ከሞት መነሳቱ ሁሉ ታሪካዊ ማረጋገጫ በመኖሩ፥ እኛም በትክክል ኢየሱስ ማን እንደሆነ እናዉቃለን። በደፈናዉ ኢየሱስ የሚሉት ኖሮ ነበር፥ከሚል ግምታዊ አስተሳሰብ ወጥቶ፤ ስለእርሱ የበለጠ መሠረታዊ እዉነታዎችን ለማወቅ (ስለእርሱ የበለጠ ለማመን)፤ ተጨማሪ እርምጃዎችን መዉሰድና መትጋት፤ እምነታችንን ይጨምራል፤ ማስተዋልና ጥበብንም ያበዛልናል። እግዚአብሔር ሁሉንም ሊሰጠን መልካም ፈቃዱ ነዉ።ኢየሱስን ተስፋ የምታደርግ ሆይ፥ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ተመለስ፥በትኅትናም ዝቅ ብለህ፥ የኢየሱስን ማንነት በትክክል ለማወቅ በብርቱ ፈልግ። በዚህ ዓለምና በሁኔታዎቿ ሁሉ ላይ የሚታይ ልዩነትን የሚያመጣዉ ይህ እዉነት፥ እርሱዉ ክርስቶስ ነዉና።

# ማጠቃለያ

- ኢየሱስ ማን ነዉ በሚለዉ ፅንሰ ሃሳብ ላይ ማንም ሰዉ ገለልተኛ ሊሆን አይችልም። እርሱ ጌታ ነዉ (እርሱም እንዳለዉ) ወይም ደግሞ ዮሐንስ 10:20 ላይ ተቃዋሚዎቹ እንደሚሉት፥ ዉሸታም፥ ወይም እብድ ነዉ። አንተስ በየትኛዉ ሃሳብ ትስማማለህ?
- ልክ መጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ እንደተጻፈዉ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ እንደኖረ ታሪካዊ ዘገባዎች አረጋግጠዋል። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን፣ከልብ በሆነ መረዳትና በጥበብ በማጥናት፣ ኢየሱስን በእዉነት ማወቅና ማን እንደሆነም

በሙላት መረዳት የእያንዳንዱ አማኝ ሃላፊነት ነዉ።

- ከግል ሃሳቤ ጋር ይስማማል፥እምነቴን ይቀበልልኛል በሚል መንፈስ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መቅረብ፤ አንዳች አይረዳም፥አደገኛም ነዉ። በጣም ከባድና አስቸጋሪ ጉዳዮች እንኳን ቢሆኑ፤ የቀድሞዉ የግል እምነታችን በመቀየሩ ምክንያት የሚገጥሙንን ተግዳሮቶች በትህትና ተቀብለን፤ መጽሐፍ ቅዱስን ትክክል ነዉ፥እዉነት ነዉ ብለን መቅረብ አለብን።

## እርስዎስ ምን ይላሉ?

- አንተስ ኢየሱስ ማን ነዉ ትላለህ?

- የቤተሰብህን ሁኔታና የራስህን አስተዳደግ ከግምት አስገባና፤ ኢየሱስ ማን ነዉ ከሚለዉ መሠረተ ሃሳብ፤ ለመጨበጥ የሚያስቸግርህ ገፅታ የትኛዉ ነዉ?

- ወንጌላትን ለማንበብ በቂ ጊዜ ብትሰጥ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በእዉነት ማን እንደሆነ አጥንተህ ትደርስበታለህ። ለመጀመሪያ ጊዜ ስለኢየሱስ ሰምተህ ገና የተጠራህም ከሆንክ፥ አዉቀኸዉ፥ አምነኸዉ፥ እንድትከተለዉ በር ይከፍትልሃል።

በተለይ ካልተገለጸ በቀር፥ ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በ 1954 ዓም ከታተመዉ የድሮዉ (KJV) ትርጉም ሲሆን፥ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ፈቃድ ተቀድቶ የታተመ ነዉ።

ሌሎች ሁሉም ይዘቶች የ © 2019 ትራንስ ዎርልድ ራዲዮ ካናዳ ነው። ይህንን ግብአት ለመጠቀም ዋጋ እስካልጠየቁ ድረስ እና ስለ ክርስቶስ አለምን መድረስን አላማዎ አድርገዉ እስከሰሩ ድረስ በፈለጉት አይነት መንገድ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ተጨማሪ የፍቃድ ዝርዝሮችን በ www.discipleshipessentials.org/licensing ይመልከቱ.